# የወጋ፡ቢረሣ፣የተወጋ፡አይረሣ፤

የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ሆይ!፦ትዕግሥትህ፡ለሰላም፡ነበር።ለገሠ፡ዜናዊ፡ግን፡የጐሣ፡ፈሊጥ፡(ፖለቲካ)፡ሲመሠርት፡ምኞቱ፡አንዱን፡ጐሣ፡፡ከሌላው፡አናክሶ፡ኢትዮጵያን፡ብጥስጥሷን፡ለማውጣት፡ነበርና፡አልተሳካለትም።በሌላ፡መልክ፡ግን፡ሕዝቧን፡ያሰቃያል።ያሥራል።ይገድላል።ችግር፡በያይነቱ፡እንዲመታት፡አድርጓል።ታዲያ፣ወጣቱም፣ጐልማሳውም፣አባቶችም፡እንዴት፡ትመለከቱታላችሁ?።ወያኔ፡ሲጫውወት፡ዝም፡ይባላል፡ወይ?።

ወያኔው፡ለገሠ፡ዜናዊና፡አበሮቹ፡ኢትዮጵያና፡ታሪኳ፡እንዲደመሰስ፡ያደረጉት፡ጥረት፡ወሰን፡የለውም።ለመሐመድ፡አላሙዲ፡የሕዝብ፡ሀብት፡የሆነውን፡የወርቅና፡የእብነ፡በረድ፡ምርት፣ሌላውንም፡የአገሪቱን፡ሀብት፡እንዲዘርፍ፡አመቻችቶለታል።አልፎ፡ተርፎ፡አርሶ፡አድሩን፡ገበሬ፡ለዘመናት፡ከሚኖርበት፡ለም፡የእርሻ፡መሬቱ፡ነቅሎ፡ለቻይና፣ለህንድ፣ለዓረብና፡ለኢንዶኔዚያ፡ሀብታሞች፡እየሸጠ፡ኪሱን፡አወፍሯል።ይህ፡የሸጥው፡መሬት፡ቀላል፡አይምሰላችሁ።እርሱና፡ወሮበሎች፡ጓደኞቹ፡ሲወርዱ፡የሚያስከትለው፡ችግር፡ኢዲ፡አሚን፡ውጋንዳ፡ላይ፡ያደረገው፡ዕድል፡እንደሚሆን፡አትጠራጠሩ።ትናትና፡ለፍሥሐ፡ደስታ፡አስቦ፡የፈታቸው፡የደርግ፡አባሎች፡እነ፡አረመኔው፡ለገሠ፡አስፋውና፡ሌሎቹም፡የደረሳቸው፡ዕድል፡እርሱንም፡ይጠብቀዋል።

ታክስ፡የማይከፍለው፡የወያኔው፡ድርጅት፡“ኤፈርት”፡ንግዱን፡እያስፋፋ፡ሲራመድ ና፡ሲዘርፍ፡ይታያል።ይኸም፡በሥልጣን፡ዝሙተኛ፡ከዓለማት፡ከሃዲ፡አምባጋነን፡የጥቅም፡ተስገብጋቢዎች፡የመጀመሪያውና፡መጨረሻው፡ያደርገዋል።ታዲያ፡በግል፡ነግዴዎች፡ላይ፡አልባሌ፡ታክስ፡እዬ፡ጫነባቸው፡ተስፋ፡የሚያስቆርጥ፡ተግባር፡መፈጸሙ፡እንዴት፡ዝም፡ይባላል?።ምንም፡ዓይነት፡ችሎታ፡ሳይኖራት፡የዚሁ፡ኤፈርት፡አመራር፡ኃላፊ፡የሆነችው፡የለገሠ፡ዜናዊ፡ሚስት፡ዘራፊዋ፡ዓዜብ፣አትራፊ፡የሆኑትን፡የንግድ፡ዕቃዎች፡እርሷ፡ብቻ፡አስመጪ፡እንድትሆን፡ማድረጓ፡ዝም፡ይባላል፡ወይ?።የምሥጢርና፡የጸጥታ፡ኃላፊ፡የነበረው፡የልጇን፡አባት፡በለገሠ፡ዜናዊ፤የጸጥታ፡ሰዎች፡ተገድሎ፡ዓዜብ፡ግን፡በሣጥናኤሉ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡ተከልላ፡ስትመጻደቅ፡እንዴት፡ቸል፡ይባላል?።የጸጥታው፡ጠባቂ፡በመሞቱ፡ያደረጉትና፡ያቀዱት፡ምሥጢር፡ለጊዜው፡ተሸሽጓል።አንድ፡ቀን፡ግን፡ይወጣል።ኧረ፡ለመሆኑ፡ምክር፡ቤቱ፡ውስጥ፡የተሰገሰጉት፡ገልቱና፡እነ፡ሆድ፡አምላኩ፡የሕዝብ፡ተጠሪዎች፡ምን፡ይሠራሉ?።እጅ፡መቀሰር፡ብቻ፡ከሆነ፡ዋጋ፡ቢሶችና፡በድኖች፡ናቸው፡ማለት፡ነው።አባቶቻችን፡ሲተርኩ፦“ባባት፡አገርና፡በሚስት፡የለም፡ዋዛ”።ብለው፡ይናገሩ፡የነበረው፡በዛሬው፡ትውልድ፡ተረስቶ፡ለሀገር፡ፍቅር፡በሌላቸው፡ተናካሽ፡ውሾች፡በለገሠ፡ዜናዊና፡በግብር፡አበሮቹ፤በዓዜብ፣በጉጉቱ፡ስብሐት፡ወልደ፡ሥላሴ፡ነጋ፣በበረከት፡ስምዖን፣ሥዩም፡መስፍንና፡ሌሎቹም፡በ፹፫፡ሚሊዮን፡ሕዝብ፡ሲቀልዱ፡ዝምታው፡ለምን፡ይሆን?።መብትህን፡ለማስከበር፡የግብፅን፣የፍልስጥኤማውያን፣ትግልና፡ቆራጥነት፡አስተውል።ምሳሌም፡አድርገህ፡ተነሣ።የ፲፱፻፺፯፡ዓመተ፡ምሕረት፤የዐድዋው፡ጀግኖች፡ሲወርድ፡ሲዋርድ፡የቆየህ፡ቅርስ፡መሆንህን፡ሳትዘነጋ፡የባንዳ፡ርዝራዥ፡አይጫወትብህ።

ለገሠ፡ዜናዊ፣በረከት፡ስምዖንና፡ሌሎቹም፡ተባባሪዎች፡የአሸባሪዎች፡ሕግ፡በማወጅ፡የሕዝብን፡መብት፡በመግፈፍ፣አሥሮ፡ለማሰቃየት፡እንዲመቻቸው፡በማቀድ፡ሕዝቡ፡ስለ፡መብቱ፡እንዳይተነፍስ፡አድረገውታል።የውጭ፡ጉዳይ፡ሚኒስትሩ፡ኃይለማርያም፡ከዓለም፡አቀፉዊ፡ምሕረት፡ተራድዖ፡ድርጅት፡(አምነስቲ፡ኢንተርናሽናል)፡እና፡ከሰብአዊ፡መብት፡አስከባሪ፡ጠባቂዎች፡

(ሂውማን፡ራይት፡ወች)፡ለደረሳቸው፡ወቀሳ፡ለጋዜጠኛ፡ጥያቄ፡መልስ፡ሲሰጥ፡-ዓይኑን፡ጨፍኖ፡ለማስ ተባበል፡ያደረገው፡ሚዛን፣የኢትዮጵያን፡የፈሊጥና፡(የፖለቲካና)፡የአስተዳደር፡ሁኔታ፡“አመሪካ”፡ ይህን፡የመሰለ፡ሕግ፡ሲያውጅ፡ምንም፡አይነገር።በኢትዮ|ጵያ፡ሲታወጅ፡ግን፡ተቃዋሚ፡ይበዛል።ብሏ ል።ልዩነቱን፡አለማወቁ፡ደደብ፡ያሰኘዋል።ዕውነቱን፡በመናገር፡ፈንታ፡ለምን፡ይዘላብዳል።መዋሸት፡ የዘወትሩ፡ጥበባቸው፡ነው።የሚውለው፡ከጌታው፡ከለገሠ፡ዜናዊ፡ጋር፡ስለ፡ሆነ፡ምን፡ይናገራል፡ተብሎ፡ ይጠበቅና!።እዬዋሸና፡እያቃዠው፡ለመኖር፡ነገሮች፡ተዋሕደውታል።ስለዚህ፡እኛ፡የምንነግረው፡የኢት ዮጵያ፡የውጭ፡ጉዳይ፡አመራር፡(ፖሊሲ)፡ኃላፊ፡ከመሆን፡ይልቅ፡ወደ፡ህዲያ፡ተመልሶ፡ከብት፡አርቢ፡ ቢሆን፡ይሻለዋል።

ኃይለ፡ማርያም፡ያልተገነዘበው፡ቢኖር፡በልመና፡የሚያስተዳድሩት፡አስተዳደር፡መሆኑን፡አያቁ ም፡ብሎ፡ሊያሞኘን፡የከጀለውን፡የማናውቅ፡መስሎታል።ነገር፡ግን፡ዴሞክራሲ፡በየትኛውም፡አገር፡እን ዲሰፍን፡እናደርጋለን፡የሚሉት፡የውጭ፡አገር፡መንግሥታት፡የዕርዳታ፡ገንዘብ፡ስለሚያፈሱላቸው።የዓ ለም፡ባንክ፡ብድር፡ስለሚሰጣቸው።ለገሠ፡ዜናዊ፡የእርሱን፡አጐብድዶ፡መኖር፡ከ፹፭፡ሚሊዮን፡የኢት ዮጵያ፡ሕዝብ፡ሰቀቀን፡አብልጦ፡መመልከቱ፡ያስተዛዝባል።ሌላው፡ቢቀር፡ሐና፡ጐሜዝ፡ያቀረቡት፡ ቁም፡ነገር፡የያዘው፡ማሳሳቢያ፣የአውሮፓ፡ኅብረት፡(ዩኒየን)፡ሳይገነዘበው፡መቅረቱ።በየጊዜው፡ዓለም፡ አቀፋዊ፡ምሕረት፡ተራድዖ፡ድርጅትና፡(አምነስቲ፡ኢንተርናሽናል)፡ሰብአዊ፡መብት፡አስከባሪ፡ጠባቂዎ ች፡(ሂውማን፡ራይት፡ወች)፡ያቀረቧቸው፡ጥያቄዎች፡ውሳኔ፡አለማግኘታቸው፤የአገሪቱን፡ገበሬዎች፡ ነቅሎ፡ለውጭ፡አገር፡ሀብታሞች፡ለም፡መሬታቸውን፡ሲሸጥና፡ገበሬው፡ከነ፡በተ፡ሰቡ፡በረሃብ፡ሲሞት፡ የተባበሩት፡መንግሥታት፡አንድም፡ዓይነት፡እርምጃ፡አለመውሰዱን፡ጊዜው፡ይፈርደዋል።ለገሠ፡ዜናዊ፡ ዘላለም፡አይኖርም።ለጊዜው፡ኢትዮጵያን፡ጐዳት።ሕዝቧንም፡አሰቃዬ።ወያኔ፡በልጽጐ፡ሌላው፡ሕዝብ፡ እዲሰቃይ፡ዕቅዱ፡መሆኑ፡የጫካ፡ውስጥ፡ዓላማው፡እንደ፡ነበረ፡ሥራው፡ያስረዳል።ወይ፡ጐንደር!፣ ወይ፡ጐጃም!፣አምቦም፡ጭፍሮቻቸውን፡በቀና፡መንፈስ፡ያሳለፈውን፡ሕዝብ፡እንዴት፡የአረመኔ፡ሥራ ን፡ይፈጽምባቸዋል?።

ጀግና፡ወልዳ፡ወልዳ፡መሀን፡ያረጋትን፣
መንግሥቱን፡መርገም፡ነው፡ለጅብ፡የሰጠንን።
ያ!፡አውሬው፡መንግሥቱ፡ከንቱ፡የሰው፡ክፉ፣
አስተላልፎን፡ሄደ፡አገር፡ለሚዘርፉ፣
ኧረ፡ውሸት፡በዛ፡ቁጭጭ፡በሉ፡ዕረፉ፣
የሆነ፡ያልሆነን፡ከምትለፈልፉ፣
ብላችሁ፡ዐውጁ፡መልክት፡አስተላልፉ፣
አለማን፡እያሉ፡ድህነት፡ተስፋፍቶ፡አገር፡እያጠፉ፤
እስከ፡መቼ፡ድረስ፡ትዕግሥት፡አስፈለገህ፣
ችላ፡አትበለው፡እንጂ፡ይሰማ፡ውሳኔህ፣
ወያኔ፡አረመኔው፡ጅብ፡ሆኖ፡እንዳይበላህ።
ለገሠ፡ዜናዊ፡አገር፡እያጠፋ፡አለማሁ፡ይልሃል፣
በሚመቸው፡መንገድ፡ንብረቷን፡ይዘርፋል።
አማራ፡ኦሮሞም፡ዝም፡ብለህ፡አትየው፣
ጠንክረህ፡ተባበር፡ኅብረት፡ጠቃሚ፡ነው፣
አገርን፡ሲያጠፋ፡ወያኔ፡ዓይንም፡የለው።
ታገል፡ጠላትህ፡ነው፡ቁረጥና፡አምርር፣
ለገሠ፡ዜናዊ፡ዓይኑ፡እስኪታወር።
እንዴት፡ዝም፡ይባላል፡ላስተዋለው፡ሰው፣
ጭካኔና፡ክፋት፡የተዋሐደው፣
ወያኔው፡ለገሠ፡በውርደት፡ያበጠው፣
የጫካውን፡አድማ፡ልቦናው፡ሲያውቅርው፣
ያገር፡ባህል፡ሳይሆን፡አስጠያፊ፡ቃል፡ነው፣
ስድብና፡ዘለፋን፡ክህነት፡ያድረገው።
ተዋርዶ፡አዋራጁን፡አንርሳው፡ክህደቱን፣
ለዓረብ፡ሐብታሞች፡የተናገረውን፣
ውሸታም፡ከሃዲ፡አያውቅም፡አገሩን።
ከኢትዮጵያ፡ሳይሆን፡ዘር፡ትውልዱ፡የመን፣
አተርፋለሁ፡ብሎ፡የቀባጠረውን፣
አይርሳው፡ድርጊቱን፡የመሸጥ፡አገሩን፣
ስለዚህ፡ክህደቱም፡በሚያስተማምን፣
የእግዚአብሔር፡ኃይል፡ይቅጣው፡ዘመን፡ከዘመን።

ትዕግሥት፡ቆይታ፡ታሸንፋለች።ጊዜው፡ ቅርብ፡ነው።የነፃነትና፡ፍትሕ፡መታወጃው፡እሩቅ፡ አይደለም።

## ኢትዮጵያ፡ለዘላለም፡ትኑር።

ከዜናማርቆስ፡መርሐ፣ካናዳ።
እ፡ጦማር፡- zienamarqos@yahoo.com